# የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የቅርስ ውሰት መመሪያ ቁጥር 482/2013

መጋቢት 2006 ዓ.ም.

<u>አዲስ አበባ</u>

# መመሪያ ቁጥር 482/2013

## የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

## የቅርስ ውሰት መመሪያ

ቅርሶችን ከሌሎች አቻ ማዕከሎች ወይም ሙዚየሞች ጋር በመዋዋስ ፣በመደጋገፍ እና የወዳጅነት ትስስርን በመፍጠር ለጥናትና ምርምር፣ ለዓውደ ርዕይ፣ ለትምህርትና ለመሳሰሉት መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የቅርስ ስብስብ ማዕከሎች ቅርስን በጊዜያዊነት ሊዋሱና ሊያውሱ የሚችሉበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የቅርስ ውሰት መመሪያ ቁጥር 482/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 ነው፡፡
2. በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 3 የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህም መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
3. **"ውሰት"** ማለት ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ ቅርስን ማዋስ ወይም በጊዜያዊነት መስጠት ነው፡፡
4. **"ቅሪተ አካል"** ማለት በአሰሳ ወይም በቁፋሮ የተገኘ የሰው፣ የእንስሳ ወይም የዕፅዋት ቅሪት ነው፡፡

5. **"አስተሻሸግ"** ማለት ለማጓጓዝ አመቺ በሆነና ቅርሶችን በማይጐዳ መንገድ እንክብካቤ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የሚከናወን የማሸግ ሂደት ነው፡፡
6. **"የመድን ዋስትና "** ማለት ከስብስብ ማዕከሉ በውሰት የሚወጣ ቅርስ የዋስትና ተመን ወጥቶለት ለሚደርስበት ማንኛውም ጉዳት በካሣ መልክ የሚሰጥ የቅርሱ ዋስትና ነው፡፡
7. **"የስብስብ ማዕከል"** ማለት የተለያዩ ቅርሶች ተሰባስበው የሚጠበቁበት ፣ እንክብካቤ የሚደረግበት፣ የሚደራጁበትና ለቀጣይ ጥናትና ምርምር ዝግጁ የሚሆኑበት ክፍል ነው፡፡
8. **"የቅርስ ደህንነት ጥበቃ"** ማለት በውሰት የተሰጠው ቅርስ በቆይታው ወቅት ሊደርግለት የሚገባ ጥበቃ፣ እንክብካቤ ወይም ጥንቃቄ ነው፡፡
9. **"ውሰት ሰጭ"** ማለት በውሰት የሚተላለፈው ቅርስ ባለይዞታ ወይም ሕጋዊ ተወካይ ነው፡፡
10. **"ውሰት ተቀባይ"** ማለት ቅርሱን በውሰት የሚወስደው /የሚቀበለው/አካል ነው፡፡
11. **"ፈቃጅ አካል"** ማለት ቅርሶች በውሰት እንዲተላለፉ ፈቃድ የሚሰጥ የቅርስ ባለይዞታ ወይም በአዋጁ አንቀፅ 27 መሠረት ሥልጣን የተሠጠው አካል ነው፡፡
12. **"የቴክኒክ ftድን"** ማለት በውሰት የሚወጡ ቅርሶችን ለመወሰን ከመረጣው ጀምሮ አጠቃላይ ሁኔታዎችን መርምሮ ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ በዚህ መመሪያ የሚቋቋም ftድን ነው::
13. **“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር”** እንደቅደም ተከተላቸው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
14. **“ባለሥልጣን”** ማለት የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፡፡
15. **“ሰው”**ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
16. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

በውሰት ወቅት ቅርሶች በአግባft ተጠብቀውና ደህንነታቸው ተረጋግጦ ለሣይንስና ምርምር፣ ለኢኮኖሚያዊ ልማትና ለባህል ልውውጥ ዘለቄታዊ አስተዋጽዖ እንዲያበርክቱ ማስቻል ነው፡፡

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ አዋጁ በሚሸፍናቸው ማንኛቸውም በውሰት በሚሰጡ ቅርሶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ቅርስን ስለማዋስ

5. <u>ቅርሶችን በሀገር ውስጥ በውሰት ስለማውጣት</u>

1. ቅርሶች በውሰት የሚንቀሳቀሱት በባለሥልጣኑ ወይም በሌሎች የቅርስ ባለይዞታዎች ዘንድ የማይገኙ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በምርምር ተቋማት ወይም በግለሰብ ተመራማሪዎች ለሚደረግ ጥናትና ምርምር ወይም ለትምህርት ወይም ለዓውደ ርዕይ ወይም ለጥበቃና ለእንክብካቤ ሥራ ብቻ ይሆናል፡፡
2. ቅርሶች በውሰት እንዲሰጡ ሲፈቀድ ወይም ሲመረጡ በተቻለ መጠን በውሰት ቢሰጡ ሊበላሹ የማይችሉና በዓይነታቸው አንድ ብቻ ያልሆኑ መሆን አለባቸው፡፡ ሆኖም ለሀገር ገፅታ ግንባታና ለሣይንሳዊ ጥናትና ምርምር የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ ጠቃሚ በሚሆንበት ጊዜና ይህም በቴክኒክ ቡድኑ ታይቶ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ሲያገኝ ዓይነታቸው አንድ ብቻ ቢሆንም ሊፈቀድ ይችላል፡፡
3. ተዋሹ አካል የተዋሰውን ቅርስ ያለ አዋሹ ፈቃድ እና ዕውቅና ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት ወይም ለንግድ ዓላማ ማዋል አይፈቀድለትም ፡፡
4. በባለሥልጣኑ ውስጥ የሚደረግ የእርስ በእርስ ቅርስ ውሰት በሚመለከተው የስብስብ ማዕከል ፈቃድ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
5. ቅርሶች ለሀገር ውስጥ ውሰት የሚወጡት ከባለሥልጣኑ በሚሰጥ የጽሑፍ ፈቃድ መሠረት ይሆናል፡፡
6. ቅርሶች በሀገር ውስጥ በውሰት ሲወጡ በአዋሹና በተዋሹ መካከል የሚፈረም አጠቃላይ የቅርሶቹን ይዘትና ዝርዝር መረጃ እንዲሁም የተዋዋዮችን መብትና ግዴታ የሚያሳይ ደረጃውን የጠበቀ ውል ባለሥልጣኑ ያዘጋጃል፡፡
7. በውሰት የወጡ ቅርሶችን ከቦታ ቦታ ማዛዋወር አስፈላጊ ሲሆን በቅድሚያ የአዋሹን አካል ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

8. በውሰት የሚወጡ ቅርሶች ክፍያ የሚኖራቸው ከሆነ የክፍያው መጠን አዋሹና ተዋሹ በሚወክሏቸው ባለሙያዎች በጋራ ተጠንቶ በሚደረስበት ሥምምነት መሠረት ይፈፀማል፡፡
9. ውሰት ሰጪው ቅርሶች በውሰት ከመውጣታቸው በፊት ተዋሹ አካል ለሚዋሰው ቅርስ ጥበቃና ደህንነት አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላቱን እና ቅርሶችን ለመዋስ ምቹና አሳማኝ ሁኔታዎች መኖራቸውን በቅድሚያ ያረጋግጣል፡፡
10. ቅርሶች በውሰት የሚሰጡት የውሰቱን ዓላማ ታሳቢ በማድረግ ከ3 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል፡፡ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት እስከ 2 ዓመት ለሚሆን ተጨማሪ ጊዜ ውሉ ሊታደስ ይችላል፡፡ በዚህም ወቅት ዋስትናው አብሮ መታደስ አለበት፡፡

## 6. ቅርሶችን በውሰት ወደ ውጭ ሀገር ስለማውጣት

1. ቅርሶችን በውሰት ከሀገር ማውጣት አይቻልም፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠው ቢኖርም ቅርሶች ለሣይንሳዊ ጥናት፣ ለባህል ልውውጥ ወይም ለዓውደ ርዕይ (ኤግዚቢሽን) ሚኒስትሩ ሲፈቅድ በጊዜያዊነት ከሀገር ሊወጡ ይችላሉ፡፡
3. ቅርሶችን በውሰት ወደ ውጭ ሀገር እንዲወጡ ሚኒስትሩ ሲፈቅድ የሚከተሉትን መርሆች መሠረት አድርጎ መሆን ይኖርበታል፡-
   ሀ. የቅርሶቹ ወደ ውጭ መውጣት ለሀገሪቱ መልካም ገፅታ ግንባታ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽዖ አለው ተብሎ ሲታመንበት፣
   ለ. ቅርሶቹ በሀገር ውስጥ በሚገኝ ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ሊደረግባቸው የማይችሉ ሆኖ ሲገኝ፣
   ሐ. የቅርሶቹ መውጣት ለደህንነታቸው ምንም ዓይነት ሥጋት የማይፈጥር መሆኑ ሲረጋገጥ፣
   መ. በመመሪያው መሠረት የተቀመጡ መሥፈርቶች መሟላታቸው ሲረጋገጥ፡፡
4. ሚኒስትሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፣ የቅርሶችን በውሰት ወደውጪ መውጣት ከመፍቀዱ በፊት ውሰቱ ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት የባለሙያዎች ኮሚቴ በማቋቋም ሊያስጠና ይችላል፡፡

5. ቅርሶች ወደ ውጭ ሀገር በውሰት ከመውጣታቸው በፊት የሀገሪቷን ጥቅም በሚያስከብር መልኩ ተዘጋጅቶ፤ አጠቃላይ የቅርሶቹን ይዘትና ዝርዝር መረጃ እንዲሁም የተዋዋዮችን መብትና ግዴታ በግልጽ የሚያሳይ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ውል በአዋሹና በሚኒስትሩ መካከል መፈረም ይኖርበታል፡፡
6. በአንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ (3)፣ (7)፤ (8)፣ (9)፣ እና (10) የተቀመጡት ድንጋጌዎች ቅርሶች ከሀገር ውጭ በውሰት በሚወጡበት ወቅትም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 7. የውሰት ተቀባይ ግዴታዎች

ማንኛውም ውሰት ተቀባይ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. ለተዋሰው ቅርስ ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ የማድረግ፤
2. ቅርሱን ለተዋሰበት ዓላማ ብቻ የማዋል፤
3. ባለሥልጣኑ ወይም የቅርሱ ባለቤት ለሚያደርጉት የቅርስ ቁጥጥርና ጥበቃ ተግባር ተባባሪ የመሆን፤
4. የተዋሰውን ቅርስ በውል በገባው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመመለስ፤
5. የቅርሱን ይዘትና ሁኔታ በሚመለከት ለውሰት ሰጪ ወቅታዊ ሪፖርት የማቅረብ፤
6. ስለቅርስ አያያዝና አጠቃቀም የወጡ ህጎችን የማክበር፡፡

## 8. የውሰት ሰጪ ግዴታዎች

ማንኛውም ውሰት ሰጪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. ቅርሶች በውሰት ሲሠጡ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ የማሳወቅ እና ውሰቱን በባለሥልጣኑ በሚዘጋጀው ውል መሠረት የመፈፀም፤
2. በውሰት የተሰጡ ቅርሶች ይዞታን በሚመለከት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ፤
3. በውል መሠረት የተቀመጠው የቅርስ ውሰቱ ጊዜ ሲያልቅ ቅርሱን የማስመለስ፤
4. በውሰት የወጡ ቅርሶች ሲመለሱ በውሰቱ ወቅት የተፈረመውን ውልና የቅርሱን መረጃ መሠረት በማድረግ ትክክለኛነታቸውን የማረጋገጥ፤
5. ቅርሱ በቆየበት ወቅት ያሉትን መረጃዎች የመያዝና የመሰነድ፡፡

# ክፍል ሦስት

# የቴክኒክ ﬁድን ስለማቋቋም

## 9. በውሰት የሚሰጡ ቅርሶችን ስለመወሰን

1. በውሰት የሚወጡ ቅርሶችን ለመወሰን ከመረጣው ጀምሮ አጠቃላይ ሁኔታዎችን መርምሮ ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የቴክኒክ ﬁድን ይቋቋማል::
2. የቴክኒክ ﬁድኑ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ፤

   ሀ. ቅርሱ ያለበት የስብስብ ማዕከል ኃላፊ.....................
   ሰብሳቢ ለ. ጉዳዩ የሚመለከተው
   ባለሙያ................................ አባል ሐ. የቅርስ
   ዶክሜንቴሽን ባለሙያ..............................አባል
   መ. የቅርስ ቁጥጥርና ክትትል ባለሙያ...........................አባልና ጸሐፊ

## 10. የቴክኒክ ﬁድኑ ስብሰባ

1. ﬁድኑ መደበኛ ስብሰባውን እንደአስፈላጊነቱ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ከﬁድኑ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. የﬁድኑ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፡፡ ድምፁ ለሁለት እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡:፡
4. ﬁድኑ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 11. የቴክኒክ ﬁድኑ ተግባርና ኃላፊነት

1. የቅርስ ውሰት ጥያቄ ሲቀርብ በመሥፈርቶቹ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
2. የውሳኔ ሃሳብ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፡፡
3. ቅርሱ በውሰት ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚመለስበት ጊዜ ድረስ ያለበትን ሁኔታ ይከታተላል፡፡
4. በየዓመቱ በውሰት የተሰጡ ቅርሶችን ዝርዝር የያዘ ሰነድ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል እንዲሰራጭ ያደረጋል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለቅርሶች መድን ዋስትና፣ አያያዝ እና ክትትል

## 12. ስለመድን ዋስትና

1. በውሰት ለሚወጡ ቅርሶች በዓይነትና በደረጃቸው ላይ የተመሠረተ የመድን ዋስትና ይገባላቸዋል፡፡
2. ለቅርሶች የሚገባው የመድን ዋስትና በማጓጓዝ ወቅት ለሚደርስ አደጋ፣ በስርቆት፣ በቃጠሎ፣ በድንገተኛ የሰው ሠራሽ እና የተፈጥሮ ክስተት ለሚደርስ ውድመት ሽፋን መስጠት አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅርሶች በውሰት ሲንቀሳቀሱ ተዋሹ አካል ለቅርሶች ደህንነት አመቺና ፈጣን የሆነ የትራንስፖርት ዘዴ መጠቀም ይኖርበታል፡፡
4. በሀገር ውስጥ ለሚደረግ የቅርሶች ውሰት የመድን ዋሰትናው በሀገር ውስጥ በሚገኙ የመድን ዋስትና ሰጪ ድርጅቶች በኩል ይሸፈናል፡፡
5. ከሀገር ውጭ ለሚደረግ የቅርሶች ውሰት ዋስትና፤ ቅርሶቹ የሚፈለጉበት ቦታ እስኪሚደርሱ ድረስ በሀገር ውስጥ የመድን ዋስትና ሰጪ ድርጅቶች የሚሸፈን ሲሆን፣ በውሰት የቆይታ ጊዜያቸው እና ወደ ሀገር በሚመለሱበት ወቅት በውጪ ሀገር የመድን ዋስትና ሰጪ ድርጅቶች በኩል የሚሸፈን ይሆናል፡፡
6. በውሰት የሚወጡ ቅርሶች የመድን ዋስትና ተመን በቅርሱ ባለይዞታና በመድን ዋስትና ሰጪ ድርጅቱ በጋራ ሥምምነት ይወሰናል፣ ወጪውም በተዋሹ አካል የሚሸፈን ይሆናል፡፡
7. በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ 1 እሰከ 6 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ ሚኒስቴሩ በራሱ መርሐ ግብር መሠረት ለዓውደ ርዕይና ለመሣሰሉት ተግባራት ቅርሶችን ከባለሥልጣኑ የስብስብ ማዕከል ሲያወጣ የመድን ዋስትና መግባት አይጠበቅበትም፡፡

## 13. በቅርሶች ላይ ስለሚደርስ ጉዳት

1. በውሰት በወጡ ቅርሶች አያያዝ ጉድለት ምክንያት ችግር እንደደረሰ ከታወቀ ወይም ጥቆማ ከቀረበ ቅርሱን የሚያውሰው ወገን ጉዳዩን የሚያጠና የባለሙያዎች ቡድን ወደ ሥፍራው ይልካል፣

2. የተላከው የባለሙያዎች ቬድን ዝርዝር ጉዳዮችን በማጥናት አጠቃላይ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፡፡
3. የባለሙያዎቹ ቬድን ቅርሱ ወደሚገኝበት ሥፍራ ተንቀሳቅሶ የተጠቀሰው ችግር መፈጠሩን ካረጋገጠ አጠቃላይ ወጭው በተዋሹ አካል የሚሸፈን ይሆናል፡፡
4. ቅርሱ ላይ ጉዳቱን ያደረሰ አካል ተገቢነት ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 14. በውሰት ስለሚወጡ ቅርሶች አስተሻሸግ

1. በውሰት የሚወጡ ቅርሶች የአስተሻሸግ ሁኔታ ለቅርሶቹ ደህንነት አመቺ መሆን አለበት፡፡
2. በማሸጉ ሂደት ቅርሱ የሚወጣበት ስብስብ ማዕከል ባለሙያዎች የቅርብ ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡
3. የቅርሱ አስተሻሻግ ሁኔታ ለቅርሶቹ ደህንነት አመቺ መሆኑን የቅርሱ ስብስብ ተቋም በቅድሚያ ያረጋግጣል

## 15. ለዓውደ ርዕይ ስለሚዋሱ ቅርሶች

ለዓውደ ርዕይ በውሰት የሚወጡ ቅርሶች በባህሪያቸው ልዩ ትኩረት ስለሚያስፈልጋቸው የሚከተሉት ጥበቃና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡-

1. ቅሪተ አካል፣ አልባሳት፣ልዩ ልዩ ቁሳቁስና መጣሪያዎች፣የሥነ ጥበብ ውጤቶች ለፀሐይ፣ ለዝናብና ለአቧራ በማይጋለጡበት ቦታ ወይም በማሳያ ሳጥን መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ቅርሶቹ በሚጐበኙበት ወቅት በእጅ እንዳይነኩ በማድረግ አመቺ በሆነ ሁኔታ ተቀምጠው መታየት ይኖርባቸዋል፡፡
3. ቅርሶቹ ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውና በፎቶ ማንሻ ፍላሽ/መብራት/ የሚጎዱ ከሆነ በሥምምነት ውሉ ላይ ተገልጾ መተግበር ይኖርበታል፡፡

## 16. ክትትልና ቁጥጥር ስለማድረግ

1. ቅርሶቹን የማዋሱ ሂደት ከተከናወነ በኋላ ለቅርሶቹ ደህንነት ሲባል ተከታታይ ጥበቃ ማድረግ እንዲያስችል በአዋሹ አካል ክትትልና ቁጥጥር ወይም ጉብኝት ይካሄዳል፡፡
2. ተዋሹ አካል በራሱ ፍላጎት ቴክኒካዊ የባለሙያዎች ጉብኝት እንዲደረግ ሲፈልግ አስፈላጊ የሆኑ የጉዞና የቆይታ ወጪዎችን የሚሸፍን ይሆናል፡፡

3. ባለሥልጣኑ ቅርሶች በውሰት ወደ ውጭ ሀገር በሚወጡበት ጊዜ፤ የሚገኙበትን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡፡
4. ባለሥልጣኑ በውሰት ወደ ውጭ ሀገር የወጡ ቅርሶች እንደተመለሱ ለሚኒስትሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህ መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 18. ቅጣት

ይህንን መመሪያ የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

### 19. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው መመሪያዎች

ይህ መመሪያ በሸፈናቸው ጉዳዮች ላይ ማንኛውም ሌላ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራሮች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም ፡፡

### 20. መመሪያውን ስለማሻሻል

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### 21. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 22 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡